AGING AND LONG-TERM SUPPORT ADMINISTRATION
PO BOX 45600
OLYMPIA WA 98504-5600

# የአዋቂዎች መከላከያ አገልግሎቶች፤ የእርስዎ መብቶች

**Adult Protective Services: Your Rights**

ከመጣል፣ ከመጎሳቆል፣ ከገንዘብ ብዝበዛና ቸል ከመባል ነፃ የመሆን መብት አሎት። መጣል፣ መጎሳቆል፣ የገንዘብ ብዝበዛ ወይም ቸልተኝነት እንዳጋጠመዎት ለማመን የሚያስችል ምክንያት ካለ የሚከተሉትን የማድረግ መብት አለዎት፡

1. ለማህበራዊና ጤና አገልግሎቶች መምሪያ (DSHS) እና ለህግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት ያድርጉና ለምርመራው ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ብለው ያመኑትን ማንኛውንም መረጃ ያካፍሉና ጠቃሚ መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ብለው የሚያምኑትን ሰዎች ይለዩ።
2. መጣል፣ ጥቃት፣ የገንዘብ ብዝበዛና ቸል መባልን በመጠቆምዎ ወይም ለጥቆማው ምክንያት በመሆንዎ ከበቀል ነጻ መሆን።
3. በተገቢ ክብር መያዝና ስነ-ስርዓት ባለው ቋንቋ መግባባት።
4. ጥቆማ ሲያደርጉ እንዲሁም በምርመራና በአስተዳደራዊ ሂደቶች ወቅት ማድረግ ለማይችሉት ሁኔታዎች በቂ መጠለያ ማግኘት።
5. የመጣል፣ ጥቃት፣ የገንዘብ ብዝበዛና ቸል መባል ያደረሰብዎትን ማንኛውም ሰው ቤትዎ ውስጥ እንዳይቆይ፣ ከእርስዎ ጋር እንዳይገናኝ ወይም ገንዘብዎትንና ንብረትዎን እንዳያገኝ የሚያደርግ ትዕዛዝ መጠየቅ።
6. ከDSHS መረጃ ማግኘት እንዲሁም የሚከራከር፣ የሚመረምር ወይም እርምጃ የሚወስድ የሌላ ኤጀንሲ ጥቆማ ማግኘት።
7. ስለምርመራው፣ ሂደቱ፣ የፍርድቤት እርምጃዎችና ውጤቶችን እርስዎ ተጠቂ የሆኑበትን ጉዳይ ከያዘው ኤጀንሲ ማወቅ።
8. ደህንነቱ የተጠበቀ ዕቅድ፣ ምርመራና አቤቱታ መስማት ሂደት ላይ እገዛ ለማግኘት ለክርክርና የህግ እገዛ ጥቆማ መጠየቅ።
9. ስለምርመራ ወይም ሂደቶች በመደበኛ ወይም ያለመደበኛ ሂደት ለDSHS ቅሬታ ማቅረብና ፈጣን ምላሽ ማግኘት።

**የመጎሳቆል፣ የመጣል፣ የቸል መባል፣ ራስን ችላ ማለት ወይም የገንዘብ ብዝበዛ ሪፖርት ለማድረግ ወይም መረጃ ለመጠየቅ፣ ይደውሉ፡**

**የተማከለ የመግቢያ ድምጽ/TTY ተደራሽ 1-877-734-6277 / TTY 1-833-866-5595**

**1-866-EndHarm (1-866-363-4276)**

የአካባቢያዊ መገኛ መረጃ፡